የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ—ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No.2
ADDIS ABABA–14th October, 2003

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፪/፲፱፻፺፮ ዓ.ም
የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓት አዋጅ ................. ገጽ ፪ሺ፬፻፯

CONTENTS

Proclamation No. 372/2003
The Proclamation to Provide for a Warehouse Receipts System ...................................... Page 2407

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፪/፲፱፻፺፮
## የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በሀገሪቱ የግብርና ምርት ውጤቶች አቅርቦት ከፍላጎት በጣም ሲልቅ ገበሬው ምርቱን በርካሽ ዋጋ ከሚሸጥ ምርቱን ለዕቃ አስቀማጮች በደረሰኝ የሚያስረክብበት እና መልሶ የሚረከብበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ ፤

ሥርዓቱ በዕቃ አስቀማጩ እና በአደራ ሰጪው መካከል በሕግ ፊት የፀና ውል ለመደረጉ ማረጋገጫ ስለሚሆን ፤ አስቀማጩ በማከማቻ ባስቀመጠው ምርት ላይ ያለውን መብት ለገዥዎች ማስተላለፍ ከፈለገ ደረሰኙን በማስረከብ ብቻ ሽያጭ የሚፈፀም በትን ሥርዓት መመሥረት ለአምራቹ ጠቀሜታ ስላለው ፤

በተለይም ይህ ዓይነቱ ሥርዓት ዕቃውን ወይም የግብርና ምርት ውጤቱን በማከማቻ ቤት በማስቀመጥ የተቀበለውን ደረሰኝ መያዣ በማድረግ ከባንክ ወይም ከመሰል አበዳሪ ተቋማት ለመበደር ስለሚያስችል ፤

ሥርዓቱ የግብርና ምርቶችን የዋጋ ውጣ ውረድ አደጋዎችን ለመከላከል ፤ በደረጃ ላይ የተመሠረተ የተቀላጠፈ የግብርና ምርቶች ግብይት ለማስፈንና የንግድና ፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን እንዲስፋፉ ስለሚረዳ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፪/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## *PROCLAMATION NO.372/2003.*
## *PROCLAMATION TO PROVIDE FOR A WAREHOUSE RECEIPTS SYSTEM*

WHEREAS, it has been necessary to introduce a system that enables the farmer whenever supply exceed demand to deliver his products to the warehouseman upon receipt of document of title to the products and to reclaim his products;

WHEREAS, the producer benefits from such a system, that constitutes a valid contract between the bailee and the bailor, which entitles the latter to transfer his rights over the stored products to any buyer by simple delivery of the receipt;

WHEREAS, the system enables the bailor to borrow money from banks or similar lending institutions upon offering warehouse receipt as collateral;

WHEREAS, the system insulates the producer from price shocks; promotes efficient marketing of standardized agricultural products and financial activities;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:–

### *PART ONE*
### *General Provisions*

1. *short Title*

This Proclamation may be cited as "The Proclamation to Provide for a Warehouse Receipts System No. 372/2003."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 5.15

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ፦

፩· "የግብርና ምርት" ማለት ሚኒስትሩ ወይም ሚኒስቴሩ የሚሰይመው አካል በተለያዩ ጊዜያት የግብርና ምርት ነው ሲል የሚወስነው ምርት ማለት ነው ፤

፪· "ዕቃ አስቀማጭ" ማለት በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ሠነድ የግብርና ምርት ውጤቶችን ጨምሮ ዕቃዎችን ተቀብሎ የሚያስቀምጥና ለአደራ ሰጭው ወይም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ከአደራ ሰጭው መብት ለተላለፈለት ሰው ዕቃዎቹን መልሶ ለማስረከብ ግዴታ የሚገባ ሰው ማለት ነው ፤

፫· "አደራ ሰጭ" ማለት ዕቃ በሌላ ጊዜ ለመውሰድ ፤ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ ፤ ለአበዳሪ ተቋም ወይም ለሌሎች ሰዎች በመያዣነት ለመስጠት በማሰብ በራሱ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ አማካኝነት ዕቃውን በዕቃ ማከማቻ ቤት የሚያስቀምጥ ሰው ማለት ነው ፤

፬· "የዕቃ ማከማቻ ውል" ማለት ዕቃ እየተቀበለ በማከማቻ ቤት ለማስቀመጥ አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፈቃድ የተሰጠው ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ለአደራ ሰጭው ወይም ከእርሱ ዕቃውን ለገዛው ወይም ዕቃውን በመያዣነት ለተቀበለው ሰው ጥቅም ሲል ዕቃውን ተቀብሎ ለማስቀመጥ ግዴታ የሚገባበት ውል ማለት ነው ፤

፭· "ማስረከብ" ማለት አደራ ሰጭው የዕቃዎቹን ባለይዞታነት በራሱ ፈቃድ ለባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ የሚያስተላልፍበት ፤ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱም ዕቃዎቹን ለአደራ ሰጭው ፤ ከእርሱ መብት ለተላለፈላቸው ወይም የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙን በመያዣነት ለተቀበሉ ሰዎች መልሶ የሚያስረክብበት ሂደት ማለት ነው ፤

፮· "ሰነድ" ማለት አንድን ፍሬነገር በመረጃነት ለማስቀረት ሲባል በፊደል ፤ በአኃዝ ፤ በምልክት ወይም ከእነዚህ ከአንዱ በላይ በሆነ መንገድ ፍሬነገሩ የሚገለጽበት ወይም የሚብራራበት ማስረጃ ማለት ነው ፤

፯· "የሸቀጥ ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ" ማለት በዘወትር የንግድና የፋይናንስ አሠራርና ልማድ ሰነዱን የያዘው ሰው ሰነዱንና በሰነድ የተመለከቱትን ዕቃዎች ለመቀበል ፤ ይዞ ለማቆየት ወይም ለሌላ ለማስተላለፍ የሚያስችል መብት የሚያገኝበት በጽሑፍ የተመዘገበ ማስታወቂያ ፤ መለያ ወይም መግለጫ ማለት ነው ፤

፰· "የኤሌክትሮኒክ ሰነድ" ማለት በኤሌክትሮኒክ ፤ በማሳያ ፤ ወይም በመሰል ዘዴዎች የወጣ ፤ የተላከ ፤ የደረሰ ወይም የተቀመጠ ሰነድ ማለት ሲሆን በኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ ፤ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት ፤ በቴሌግራም ፤ በቴሌክስና በቴሌኮፒ የወጣ መረጃን ይጨምራል ፤

፱· "ተተካኪ ዕቃዎች" ማለት በተፈጥሮ ባህሪያቸው ወይም በልማዳዊ የንግድ አሠራር ዕርስ በእርሳቸው ሊለዋወጡና ሊተካኩ የሚችሉ ዕቃዎች ማለት ነው ፤

፲· "ዕቃዎች" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የዕቃ ማከማቻ ውል ሊደረግባቸው የሚችሉ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ማለት ነው ፤

፲፩· "አምጭ (ያዥ)" ማለት በስሙ ወይም ላዘዘለት ተብሎ የተሰጠውን ፤ ስሙ ተጽፎ ወይም ሳይጻፍ በጀርባ ፊርማ የተላለፈለትን ፤ ወይም በእጁ በማድረግ ብቻ መብት የሚያገኝበትን የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የያዘ ሰው ማለት ነው ፤

2. *Definitions*

Unless the context requires otherwise; in this Proclamation:–

1) ''Agricultural Product'' means a product as may; from time to time be determined as an agricultural product by the Ministry or its designate.

2) ''Bailee'' means a person who, by a warehouse receipt or similar other instrument; acknowledges possession of goods; including agricultural products; and undertakes to deliver them to the bailer or his transferee in accordance with the provisdions of this Proclamation.

3) ''Bailor'' means a person who, on his own or through a lawful agent, delivers goods to a warehouseman for the purpose of storage in the latter's warehouse with the intention of reclaiming the goods, transferring them to a third party or offering them as collateral to a lending institution or other persons.

4) ''Contract of warehousing'' means a contract whereby one party, the warehouseman, being duly licensed by the appropriate organ, undertakes to receive and store goods on behalf of either of the bailor or of the purchaser of the goods or of a person who receives it in pledge.

5) ''Delivery'' means the process of voluntary transfer of possession of goods by a bailer to a warehouseman and the redelivery thereof to the bailer his transferee or his pledgee.

6) ''Document'' means an instrument on which any matter of substance is expressed or described by means of letters, figure, marks, or by more than one of these means and intended to be used or which may be used for the purpose of recording that matter.

7) ''Document of title to goods'' means a written description; identification or declaration of goods which, in the regular course of business or financing, is treated as evidencing that the person in possession of it is entitled to receive, hold and dispose of the document and the goods it covers.

8) ''Electronic document'' means a document generated, sent, received or stored by electronic, optical or similar means including, but not limited to, electronic data interchange, electronic mail, telegram telex or telecopy.

9) ''Fungibles'' means goods of which any unit is, by nature or usage of trade, treated as the equivalent of any other unit.

10) ''Goods'' means all corporeal movables which may be subject to a contract of warehousing under this Proclamation.

11) ''Holder'' means a person who is in possession of a warehouse receipt issued or endorsed to him or to his order or to bearer or in blank.

፲፪· "የቅን ልቦና ያዥ" ማለት በሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ፣ በደረሰኙ ወይም በደረሰኙ በተመለከቱት ዕቃዎች ላይ አስቀድሞ ስለነበረ የይገባኛል ጥያቄ የሚያውቀው ነገር ሳይኖር አንድን የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ዋጋ ሰጥቶ የተቀበለ አምጭ ማለት ነው ፤

፲፫· "የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ" ማለት በጀርባ ተፈርሞበት ወይም ሳይፈረምበት በመስጠት ከአንዱ ወደ ሌላው ሊተላለፍ የሚችል የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ማለት ነው ፤

፲፬· "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደአገባቡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው ፤

፲፭· "ሰው" ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው ፤

፲፮· "የዋስትና ጥቅም" ማለት አደራ ሰጭው ለባለዕቃ ማከማቻው ወይም ለሌላ ሦስተኛ ወገን አንድ የታወቀ ግዴታ ለመወጣት ሲል ከገባው የዋስትና ግዴታ የሚመነጭና የዋስትናው ተጠቃሚዎች በአደራ ሰጭው ስም በዕቃ ማከማቻ ቤቱ በተቀመጡት ዕቃዎች ላይ የሚኖራቸው መብት ማለት ነው ፤

፲፯· "ሲስተም ፕሮቫይደር" ማለት በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኝ ሆኖ በሥራ አመራር ፤ በኤሌክትሮኒክ መረጃ አቅርቦትና አያያዝ ፤ እንዲሁም በኮምፒዩተር አሠራር በሚደገፉ የኤሌክትሮኒክ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች አማካኝነት የሚደረጉ ግንኙነቶች ስለሚካሄዱበት መንገድ ለባለዕቃ ማከማቻዎች አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ማለት ነው ፤

፲፰· "የዕቃ ማከማቻ ቤት" ማለት በባለዕቃ ማከማቻው ሕጋዊ ይዞታና ቁጥጥር ሥር ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ዕቃ የሚከማችበት ሕንጻ ወይም ተለይቶ የተከለለ ሥፍራ ማለት ነው ፤

፲፱· "ባለዕቃ ማከማቻ ቤት" ማለት የሙያ ሥራው በማድረግና ጥቅም ለማግኘት ሲል የሌሎች ሰዎችን ዕቃዎች እየተቀበለ በማስቀመጥ ንግድ ሥራ የተሠማራ ሰው ማለት ነው ፤

፳· "የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ" ማለት ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ የሌላ ሰው ዕቃ መረከቡ የተረጋገጠበት በዚህ አዋጅ መሠረት የተዘጋጀ የጽሑፍ ማስረጃ ማለት ሲሆን የኤሌክትሮኒክ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝንም ይጨምራል።

፳፩· "የማገቻ መብት" ማለት ያልተከፈሉ ወይም ቀሪ የማከማቻ ቤት ሂሣቦችን ጨምሮ ዕቃውን ለማስቀመጥ፣ ለማዘጋጀትና ለመጠቅለል ፤ ለማጓጓዝ ፤ መድን ለመግባት ፤ ለጉልበትና ሙያ ሥራ እና ለሌሎች ዕቃውን በአግባቡ ለመያዝ ወይም ለመሸጥ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተደረጉ ወጪዎችን ክፍያ አስመልክቶ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ተመልክቶ በማከማቻ ቤት በተቀመጠ ዕቃ ወይም ከዚህ ዕቃ ሽያጭ በተገኘው ሂሣብ ላይ እራሱን የማከማቻ ሰነዱን በመያዣነት የተቀበሉ ባለገንዘቦችን ጨምሮ ከማንኛውም የአደራ ሰጪ ወይም ከእርሱ መብት የተላለፈለት ባለገንዘብ ያለው የተሻለ የቅድሚያ መብት ነው ።

፫· <u>ዓላማ</u>

የዚህ አዋጅ ዓላማ ፤

፩· ማንኛውም ሰው ዕቃውን በተለይም ደረጃ የወጣለትን የግብርና ምርት በዕቃ ማከማቻ ቤቶች በማስቀመጥ የያዘውን ደረሰኝ በመያዣነት በመስጠት ገንዘብ ለመበደር እንዲችል ለማድረግ ፤



12) "Holder in due course" means a person who is in possession of a negotiable warehouse receipt for consideration, in good faith and without notice of any prior claim or defense against it.

13) "Negotiable warehouse receipt" means a warehouse receipt that is legally capable of being transferred by endorsement or delivery.

14) "Ministry or Minister" means the Ministry and Minister of Trade and Industry respectively of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

15) "Person" means any physical or juridical person.

16) "Security interest" means an interest in goods kept in warehouse obtained pursuant to a security agreement for the performance of an obligation by the bailor towards the warehouseman or a third party.

17) "System Provider" means a person wherever domiciled who provides services to a licensed warehouse operator in matters pertaining to management, to the provisions of electronic records, and to the setting up and maintenance of computer based systems to manage and record transactions in respect of electronic receipts.

18) "Warehouse" means a building or other protected enclosure in the lawful possession and exclusive control of a warehouseman in which goods are stored in accordance with the provisions of this Proclamation.

19) "Warehouseman/operator" means a person who, professionally and for gain, is engaged in the business of storing goods for others.

20) "Warehouse receipt" means a written acknowledgment drawn in accordance with this Proclamation and issued by a warehouseman purporting receipt of goods belonging to another for storage and includes electronic warehouse receipts,

21) "Rights to Lien" it is a preferential rights of the warehouse man over the goods stored in awarehouse or over the pleadgee of warehouse recipts or over the bailer or his transferee on the proceeds earned from sale of the goods, in relation to the cost incurred persuant to the provision of this proclamation to store, prepare,pack, transport, insure and for Labour and professional work and incurred to preperly handled the goods and sale, includily the unpaid and remaining warehouse cost.

3. *Objectives*

This Proclamation shall have the following objectives:

1) to enable any person store his goods and in particular standardized agricultural products in warehouses and borrow money upon delivery of the warehouse receipt as collateral;

፪· በዕቃ አስቀማጮች እና በአደራ ሰጪዎች መካከል በሕግ ፊት የፀና ውል ለመመሥረትና ሥርዓቱንም በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር ለማስቻል ፤ እና

፫· የተደራጀና የተሳለጠ የግብርና ምርቶች የግብይት ሥርዓት ለመፍጠር ነው ፡፡

፬· <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩· በልዩ ሕጎች የተመለከተ ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ አዋጅ ከዕቃ ማከማቻ ውሎች በሚመነጩና ከእነርሱም ጋር ተያያዥነት ባላቸው ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ፤

፪· አግባብነት ያላቸው የ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. የፍትሐብሔርና የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ በማሟያነት ተፈጻሚ ይሆናሉ ፡፡

## ክፍል ሁለት
## የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ስለማውጣት

፭· <u>የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ለማውጣት ስለሚችሉ አካላት</u>

፩· በመንግሥት በኩል ተገቢው ማበረታቻ እየተደረገላቸው በዚህ አዋጅ መሠረት የዕቃ ማከማቸት ንግድ ሥራ ለመሥራት የንግድ ፈቃድ ያወጡና ምዝገባ ያደረጉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ለማውጣት ይችላሉ ፤

፪· በዚህ አዋጅ መሠረት የዕቃ ማከማቸት ንግድ ሥራ ለመሥራት የንግድ ሥራ ፈቃድ ያወጣና ለዚሁም ምዝገባ ያደረገ ማናቸውም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም አክሲዮን ማኅበር ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ለማውጣት ይችላል ፡፡

፮· <u>የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ፎርም</u>

፩· ዕቃዎችን ለማስቀመጥ የተቀበለ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት አደራ ሰጭው ሲጠይቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተገለጸው ፎርም መሠረት የተዘጋጀ አንድ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ የሆኑ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች አውጥቶ ይሰጠዋል ፤

፪· አንድ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የሚከተሉትን ዝርዝር ፍሬ ነገሮች መያዝ አለበት ፤

ሀ) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የወጣው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት መሆኑን የሚያመለክት መግለጫ ፤

ለ) የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን ስም ፣ አድራሻና የምዝገባ ቁጥር ፤

ሐ) የዕቃ ማከማቻ ቤቱን ወይም ዕቃዎቹ የተቀመጡበትን ሌላ መገኛ ቦታ የሚያመለክት መግለጫ ፤

መ) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የወጣበትን ቀን ፤

ሠ) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙን የቅደም ተከተል ተራ ቁጥር ፤

ረ) የዕቃ አስቀማጩን ወይም በስሙ ዕቃ የተቀመጠለትን ሰው ስምና አድራሻ ፤

ሰ) የዕቃ ማስቀመጫ ክፍያውን ተመን ፤

ሸ) በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የተመለከቱትን ዕቃዎች ዓይነት ፣ የጥራት ፣ ደረጃና መጠን ፤

ቀ) በዕቃ ማከማቻ መጋዘን ዕቃው ገቢ በሚሆንበት ዕለት የዕቃው የዋጋ ግምት ፤

በ) ዕቃዎቹ በማከማቻ ቤቱ የሚቆዩበትን የጊዜ ገደብ፤

ተ) በቅድሚያ የተከፈለውን የአገልግሎት ሂሣብ እና ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በዕቃዎቹ ላይ ሊኖረው የሚችለውን የማገድ ወይም የዋስትና ጥቅም ወሰን የሚያሳይ መግለጫ ፤

ቸ) ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ እንደተጠየቀ ዕቃዎቹን ለማስረከብ ግዴታ እንደገባ የሚያመለክት ማረጋገጫ እና

ኀ) የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን ፊርማ ፤

2) to establish a valid contract between the bailee and the bailor and to properly direct and administer the system: and

3) to create organized and efficient marketing system for agricultural products.

4. *Scope of Application*

1) Unless otherwise expressly provided by special laws, this Proclamation shall apply to all forms of transaction arising out of and in connection with contracts of warehousing.

2) The relevant provisions of the 1960 Civil and Commercial Codes of Ethiopia shall complement this Proclamation.

## *PART TWO*
## *Issuance of Warehouse Receipts*

5. *Bodies Capable of Issuing Warehouse Receipts*

1) Being given the appropriate incentive by the Government, cooperative societies registered and licensed to undertake warehousing business pursuant to the provisions of this Proclamation, may issue warehouse receipts.

2) A Private Limitted Company, a share company or public enterprise registered and Licensed for the purpose of undertaking warehousing business in accordance with the provisions of this Proclamation, may issue warehouse receipts.

6. *Form of Warehouse Receipts*

1. Upon receipt of goods for storage, a warehouse operator shall, when requested by the bailor, issue a warehouse receipt or any number of warehouse receipts as the case may be in the form specified under Sub-Article (2) hereof.

2) Awarehouse receipt shall contain the following particulars:

(a) a statement that the warehouse receipt is issued in accordance with the provisions of this Proclamation;

(b) the name, address and registration number of the warehouse operator;

(c) the location of the warehouse or other places where the goods are stored;

(d) the date of issue of the warehouse receipt;

(e) the consecutive number of the warehouse receipt;

(f) the name and address of the person by whom or on whose behalf the goods are stored;

(g) the rate of storage charges;

(h) the kind, quality and quantity of the goods represented by the warehouse receipt;

(i) the cost of the goods at the time when it is stored at the warehouse;

(j) the time limit until when the goods are to be stored;

(k) a statement of the amount of any advance made and of any liability incurred for which the warehouse operator claims a lien or has a security interest;

(l) an undertaking by the warehouse operator to deliver the goods on demand; and

(m) the signature of the warehouse operator.

፫· ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕቃዎቹን በማስረከብና በጥንቃቄ ይዞ በማቆየት ረገድ ያለበትን ግዴታ አስመልክቶ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ላይ በደረሰኙ ተጠቃሚ የሚሆኑ ወገኖችን ግንኙነት በተሻሸለ ሁኔታ የሚገልጽ ተጨማሪ ፍሬ ነገር ማስገባት ይቻላል ።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተዘረዘሩትን ፍሬ ነገሮች በደረሰኙ ያልገለጸ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ይህን ባለማድረጉ ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊ ይሆናል። ይሁንና በዚህ ጉድለት ብቻ ደረሰኙ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አይደለም ተብሎ ግምት አይወሰድበትም ።

፭· አንድ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በዚህ አዋጅ እንደተደነገገው ከአንዱ ወደሌላው እንዲተላለፍ የሚደረግበትን አሠራር ሊያመለክት የሚችል መግለጫ የሚሰጥበት በቂ ክፍት ቦታ ሊኖረው ይገባል ፣

፮· አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አምጭ በተጠየቀበት ጊዜ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመጠየቅ አንድን ደረሰኝ ጠቅላላ ዋጋቸው ፣ የአገል ግሎት ክፍያቸውና የመቆያ ጊዜያቸው ከፊተኛው ደረሰኝ ጋር እኩል በሆነ በርካታ አነስተኛ ደረሰኞች ለመተካት ፣ ወይም አነስተኛ ደረሰኞችን አንድ ላይ በማጠቃለል በከፍተኛ ደረሰኝ ለመቀየር ይችላል ።

፯· <u>የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሕጋዊ አቋም</u>

፩· በሕግ አግባብ ተዘጋጅቶ ለአደራ ሰጭው የተሰጠ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በባለዕቃ ማከማቻ ቤቱና በአደራ ሰጭው መሀል በሕግ ፊት የሚፀና ውል ለመደረጉ ማረጋገጫ ነው ፣

፪· አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. በወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ ስለውሎች በጠቅላላውና በተለይም ስለአደራ ውሎች የተመለከቱት አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ተዋዋይ በሚሆኑ ወገኖች መሀል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ይህን አዋጅ በማሟላት ተፈፃሚ ይሆናሉ ።

፰· <u>ተደራራቢ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ስለማውጣት</u>

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠፉ፣ የተሰረቁ ወይም የተበላሹ ደረሰኞችን ለመተካት ካልሆነ በስተቀር አስቀድሞ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ለወጣላቸው ዕቃዎች ሌላ ደረሰኝ ማውጣት አይቻልም።

፪· የመጀመሪያው የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አምጭ ወይም ከእርሱ መብት የተላለፈላቸው ሰዎች በዕቃዎቹ ላይ የነበረውን መብት እንደያዙ ይቆያሉ፣

፫· ተደራራቢ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን አውጥቶ የሰጠ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ይህን በማድረጉ ምክንያት በተከታታዮቹ የደረሰኙ አምጭዎች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊ ይሆናል፣

፬· ተደራራቢ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች በተሰጡበት ተመሳሳይ ዕቃ ላይ የመጀመሪያውን አምጭ መለየት ካልተቻለ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ለሁሉም አምጭዎች በግል ኃላፊነት ይኖርበታል፣

፱· <u>የተለወጡ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች</u>

፩· በሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ላይ ያለ ክፍት ቦታ የተሞላው ይህን ለማድረግ ሥልጣን በሌለው ሰው ቢሆንም እንኳ የደረሰኙ የቅን ልቦና ያዥ በደረሰኙ የተመለከቱትን ዕቃዎች በተመለከተ ሙሉ መብት ይኖረዋል፣

፪· ሥልጣን በሌለው ሰው በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ላይ የተደረገ ሌላ ማናቸውም ለውጥ ደረሰኙ በመጀመሪያው ግዴታ መሠረት በባለዕቃ ማከማቻ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን የማድረግ ውጤት ብቻ ይኖረዋል።



3) Without prejudice to the provisions of this Proclamation pertaining to the obligation of a warehouse operator to deliver the goods on demand and to his duty of care and diligence, a warehouse receipt may contain in it any other term that better defines the relationship of the parties to the transaction.

4) Where a warehouse operator omits to include any one of the particulars specified under Sub-Article (2) hereof, he shall be liable for damages arising out of such omission provided, however, that no receipt shall be deemed not to be a warehouse receipt by reason of such omission.

5) A warehouse receipt shall provide enough space to register its negotiation thereof to some specified person in accordance with the provisions of this Proclamation.

6) Subject to reasonable service charges, a warehouse operator, may upon request by the holder of a warehouse receipt, replace a warehouse receipt with Warehouse receipts of smaller denomination which are of the like tenure and warehouse charge as the replaced one. He may likewise replace warehouse receipts of smaller denomination with greater one (s).

7. *Legal Status of a Warehouse Receipt*

1) A duly drawn up warehouse receipt delivered to a bailor shall constitute a valid contract between a warehouse operator and a bailor.

2) The relevant provisions of the 1960 Civil Code of Ethiopia on Contracts in General and on Contracts of Bailment in particular may supplement this Proclamation in governing the relationship of parties to a warehouse receipt.

8. *Over Issue of Warehouse Receipts*

1) Without prejudice to the provisions of Article 6(6) of this Proclamation, no more than one warehouse receipt shall be issued in respect of the same goods already represented by an outstanding warehouse receipt except in substitution for lost, stolen or destroyed receipts.

2) The holder of the original receipt or his transferees shall retain title to the goods.

3) A warehouse operator over issuing warehouse receipts shall be liable for damages caused to holders of subsequent warehouse receipts.

4) Where it cannot be ascertained who the original holder is, the warehouse operator responsible for the over issue shall be severally liable to all the holders.

9. *Altered Warehouse Receipts*

1) Where a blank in a negotiable warehouse receipt has been filled in by a person without authority, the holder in due course of such a receipt shall have full title on the goods represented by the instrument.

2) Any other unauthorized alteration leaves any warehouse receipt enforceable against the warehouse operator in accordance with its original terms.

፲· የጠፉ የተሰረቁና የተበላሹ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች

፩· አንድ የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሲጠፋ፣ ሲሰረቅ፣ ወይም ተበላሽቶ ጉዳት ሲደርስበት አምጭው ይህንኑ እንዳወቀ በ፳፬ ሰዓት ውስጥ ሁኔታውን በጽሑፍ ለባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ መግለጽ አለበት፣

፪· የጠፋ የተሰረቀ ወይም የተበላሸ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አምጭ ነበርኩ የሚል ሰው በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የተገለጹት ዕቃዎች እንዲሰጡት ወይም ምትክ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ እንዲሰጠው እንዲታዘዝለት ያለመዘ ግየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማመልከት አለበት። ፍርድ ቤቱም በትዕዛዙ ምክንያት ጉዳት ሊደርስበት ለሚችል ሰው ካሣ የሚሆን በቂ ዋስትና እንዲያስይዝ በማድረግ በአቤቱታው መሠረት ትዕዛዝ ሊሰጥለት ይችላል። የፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በተሰጠ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከዋስትናው መብት አገኛለሁ የሚል ወገን ካልመጣ ዋስትናው በራሱ ቀሪ ይሆናል፣

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ማስታ ወቂያ የደረሰው ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በጠፋው የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ መነሻነት ለሚጠይቅ ሰው ዕቃውን ያስረከበ እንደሆነ በዚህ አድራጎቱ ጉዳት ለሚደርስበት ሰው ኃላፊ ይሆናል።

፲፩· በፍርድ አፈጻጸም ስለሚሰጥ ማስከበር ትዕዛዝ

የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ስም ሳይሆን በሌላ ሰው ስም ወጥቶባቸው በዕቃ ማከማቻ ቤት እንዲቀመጡ የተደረጉ ዕቃዎች በባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕዳ ወይም በእርሱ ላይ በሚሰጥ የመክሰር ውሳኔ መነሻነት በፍርድ አፈጻጸም እንዲከበሩ አይደረግም።

፲፪· ተጻራሪ የሆኑ የይገባኛል ጥያቄዎች

በዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ መብት አለን ወይም በደረሰኙ የተመለከቱት ዕቃዎች ይገቡናል በማለት የተለያዩ ሰዎች ጥያቄ ሲያቀርቡና ከእነዚህ ሰዎች ለየትኛው ግዴታውን መወጣት እንዳለበት ለማወቅ ለባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ አጠራጣሪ በሚሆ ንበት ጊዜ በቂ ጊዜ ወስዶ ትክክለኛውን ባለመብት እስኪያረ ጋግጥ ወይም ይኸው እንዲረጋገጥ የኃላፊነት ይውረድልኝ አቤቱታ ለፍርድ ቤት እስከሚያቀርብበት ጊዜ ድረስ ዕቃውን የማስረከብ ግዴታውን እንዲወጣ አይገደድም።

## ክፍል ሦስት
## የባለዕቃ ማከማቻ ቤት መብትና ግዴታዎች

፲፫· የማስረከብ ግዴታ

፩· አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አውጥቶላቸው ተቀብሎ ያስቀመጣቸውን ዕቃዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) በተደነገገው መሠረት የማስረከብ ግዴታ አለበት፣

፪· የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የሚተላለፍ ሲሆን አደራ ሰጭው ዕቃውን የሚረከበው፦

ሀ) ለባለዕቃ ማከማቻው መወጣት ያለበትን ዕቃውን ከዕግት ነፃ የማድረግ ግዴታ ሲወጣ፣

ለ) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙን ለባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በመስጠት፣

ሐ) ዕቃውን መረከቡን በጽሑፍ ሲያረጋግጥ፣ ነው።

፫· የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ የማይተላለፍ ሲሆን አደራ ሰጭው ዕቃውን የሚረከበው፣

ሀ) ለባለዕቃ ማከማቻው ቤት መወጣት ያለበትን ዕቃውን ከዕግት ነፃ የማድረግ ግዴታውን ሲወጣና፣

ለ) ዕቃውን መረከቡን በጽሑፍ ሲያረጋግጥ ነው።

10. *Lost, Stolen or Destroyed Warehouse Receipts*

1) In the event of loss of, theft or injury to a negotiable warehouse receipt, the holder shall advise the warehouse operator in writing of the circumstances within twenty four hours of becoming aware of this fact.

2) A person claiming to be the holder of a lost, stolen or destroyed negotiable warehouse receipt shall forthwith apply to a court for an order for delivery of the goods or issuance of a substitute negotiable warehouse receipt. The court may grant the request upon requiring the holder to post adequate security to indemnify any one who may sustain damages as a result of the order. Such security shall by operation of the law, lapse if no one appears to claim his rights therefrom in two years following the court order.

3) A warehouse operator on whom due notice is served in accordance with the provisions of Sub-Article (1) hereof who, without a court order, delivers the goods to a person claiming under a missing negotiable warehouse receipt is liable to any person injured thereby.

11. *Attachment*

Goods kept in a warehouse for which warehouse receipts are issued in the name of a person other than the warehouse operator shall not be liable to attachment on account of debts or bankruptcy of the warehouse operator.

12. *Conflicting Claims*

Where several persons claim title to or delivery of the goods and where it is doubtful to which one of them he may discharge his obligafions under a warehouse receipt, a warehouse operator is excused from his duty to deliver the goods until he has a reasonable time to ascertain the validity of the adverse claims or until he takes a suit of interpleader before a court for the purpose of ascertaining the one with valid title.

## PART THREE
## Rights and Obligations of a Warehouse Operator

13. *Duty to Deliver Goods*

1) A warehouse operator shall deliver the goods represented by a warehouse receipt in the manner provided for under Sub-Article (2) and (3) hereof.

2) Where a warehouse receipt is negotiable, the bailor takes delivery of the goods:-

(a) by satisfying the warehouse operator's lien rights;

(b) by surrendering the warehouse receipt to the warehouse operator; and

(c) by acknowledging in writing the delivery of the goods.

3) Where a warehouse receipt-is non-negotiable, the bailor takes delivery of the goods:

(a) by satisfying the warehouse operator's lien rights: and

(b) by acknowledging in writing the delivery of the goods.

፬· አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃውን ለማስረከብ ያልፈቀደ ወይም ያልቻለ እንደሆነ ያልፈቀደበት ወይም ያልቻለበት በቂ ሕጋዊ ምክንያት ያለው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት። ይህም ምክንያት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ መሆን አለበት።

ሀ) ዕቃውን ትክክለኛ መብት ላለው ጠያቂ ያስረከበ መሆኑን፣

ለ) ዕቃውን የማግኘት ሕጋዊ መብቱን ተግባራዊ ለማድረግ ሲል ወይም ዕቃውን የማስቀመጥ ግዴታውን በሕግ መሠረት ካቋረጠ በኋላ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕቃዎቹን የሸጠ ወይም በማናቸውም መንገድ ያስወገደ ሲሆን፣ ወይም

ሐ) ፍርድ ቤት ወይም በአግባቡ የተቋቋመ የግልግል ሸንጎ ሕጋዊ ነው ብሎ በሚወስነው ሌላ ማናቸውም ምክንያት፣

፭· በቅንልቦና እና በመስኩ የተለመደውን አሠራር በትክክል በመከተል በዚህ አዋጅ መሠረት ዕቃ የተቀበለ፣ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የሰጠና ዕቃዎቹን መልሶ ያስረከበ ወይም በሌላ መንገድ ያስወገደ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ዕቃውን እንዲከማች የሰጠው ሰው ዕቃውን ለመስጠት ፣ ዕቃውን የተረከበውም ሰው ለመረከብ የሚያስችል ሥልጣን ባይኖረውም እንኳ ይህንን በማድረጉ በኃላፊነት አይጠየቅም።

## ፲፬· ጥንቃቄና ትጋት

፩· አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዕቃ ማከማቻ ቤቱ ውስጥ ለማከማቸት የሚረከባቸውን ዕቃዎች በአግባቡ የመያዝና የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፣

፪· የሥራው ባህርይ የሚጠይቀውንና ማንም ሰው በእርሱ ቦታ ቢሆን ሊያደርግ የሚገባውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ምክንያት የተከማቹት ዕቃዎች ቢጠፉ ወይም ቢበላሹ ለሚደርሰው ጉዳት ባለማከማቻ ቤቱ ኃላፊ ነው፣

፫· የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን የውል ግዴታ መጠን በማከማቻ ቤቱ ካስቀመጣቸው ዕቃዎች ትክክለኛ ዋጋ አሳንሶ የሚወስን የውል ቃል በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ ላይ መጻፍ ውጤት አይኖረውም፣

፬· ተቀብሎ ባስቀመጣቸው ዕቃዎች ላይ የመለወጥ ነገር በመታየቱ ሳቢያ ተጨማሪ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ይህንኑ በጽሑፍ ለአደራ ሰጭው ማስታወቅ አለበት።

## ፲፭· ባለመረከብና አሳስቶ በመግለጽ ስለሚደርስ ኃላፊነት

አንድ የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ሥልጣን በተሰጠው ወይም ከነገሩ አካባቢ ሁኔታ ሲታይ ሥልጣን የተሰጠው በሚመስል የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ወኪል ወይም ሠራተኛ መፈረሙ ከተረጋገጠ ዕቃዎቹ በሙሉ ወይም በከፊል በማከማቻ ቤቱ የተቀመጡ ወይም ዓይነታቸው ወይም መጠናቸው ለደረሰኙ ከተሰጠው መግለጫ የተለየ ቢሆንም እንኳ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ የደረሰኙ የቅን ልቦና ባለይዞታ ለሆነው ሰው ሙሉ ኃላፊነት አለበት።

## ፲፮· ስለማደባለቅ

፩· አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ከአደራ ሰጭው ግልጽ ፈቃድ ሳያገኝ የተቀበለውን ማናቸውንም ዕቃ በማከማቻ ቤቱ ካስቀመጣቸውና በዓይነትና በጥራት ተመሳሳይ ከሆኑ ሌሎች ዕቃዎች ጋር መደባለቅ የለበትም፣

፪· ዕቃዎቹን በቀላሉ ለመለየትና ጥያቄ በቀረበ ጊዜም ያለችግር ለማስረከብ ይረዳ ዘንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በእያንዳንዱ ደረሰኝ የተመለከቱትን ዕቃዎች ለየብቻ ማስቀመጥ አለበት፣

4) Where a warehouse operator refuses or fails to deliver the goods in accordance with the provisions of this Article, he shall bear the burden of establishing the existence of a lawful and justifiable excuse for his refusal or failure. Such excuse shall constitute any one of the following:

(a) delivery of the goods to a person whose receipt was rightful as against the claimant;

(b) previous sale or other disposition of the goods in lawful enforcement of a line or on a warehouse operator's lawful termination of storage;

(c) any other defense deemed to be lawful by a court of law or a duly constituted arbitration tribunal.

5) A warehouse operator who, in good faith and in full compliance with the standard commercial practice in the field, has received goods, issued warehouse receipts, and delivered or otherwise disposed of them in accordance with the provisions of this Proclamation shall not be held liable even though the person from whom he received the goods had no authority to deliver them or even though the person to whom he delivered the goods had no authority to receive them.

## 14. *Duty of Care and Diligence*

1) A warehouse operator shall be liable for the preservation of the goods he has received for storage;

2) A warehouse operator shall be liable for damages for loss of injury to the goods caused by his failure to exercise such care as a reasonable person would exercise under like circumstance.

3) Any provision in a warehouse receipt limiting the contractual liability of a warehouse operator to an amount less than the actual value of the goods stored shall be of no effect.

4) A warehouse operator shall inform the bailor in writing whenever the goods kept with him undergo changes that seem to call for further measures.

## 15. *Liability for Non-receipt or Misdisciption*

A warehouse operator assumes full liability to a holder in due course of a negotiable warehouse receipt notwithstanding that he did not receive the goods in part or in whole or the goods or their quality or quantity do not correspond with the description in the receipt where it is shown that the receipt is signed by an agent or employee of the warehouse operator having real or apparent authority for so doing.

## 16. *Commingling*

1) A warehouse operator may not mix goods stored in his warehouse with other goods of like kind and quality unless he obtains an express authorization from the bailor to this effect.

2) He shall separate the goods covered by each warehouse receipt in order to make way for easy identification and delivery upon demand.

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተገለጸው ቢኖርም አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ተተኪ ዕቃዎች በዓይነት፣ በጥራትና በደረጃ ተመሳሳይ ከሆኑ ከሌሎች ተተኪ ዕቃዎች ጋር ማደባለቅ ይችላል። እንዲህም በሆነ ጊዜ እንዲደባለቁ የተደረጉትን ዕቃዎች የሚያሳዩ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞች አምጭዎች የዕቃዎቹ የጋራ ባለንብረት እንደሆኑ ይቆጠራሉ፣ በያዙት የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የተመለከተውን ዕቃም የመጠየቅ መብት አላቸው።

፲፯· የዕቃ ማከማቻ ስምምነት የቆይታ ጊዜ

፩· በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ ላይ የተመለከተው ጊዜ ሲያበቃ፤ ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕቃው በስሙ ለተቀመጠለት ሰው፣ ለሕጋዊ ወኪሉ ወይም በዕቃው ላይ ሕጋዊ መብት እንዳለው ለሚታወቅ ለማናቸውም ሰው ተገቢውን ማስታወቂያ በመስጠት ያለበትን አገልግሎት ሂሣብ ከፍሎ ዕቃውን እንዲረከብ ሊጠይቀው ይችላል።

፪· ዕቃው የሚቀመጥበት ጊዜ ያልተገለጸ ሲሆን ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ዕቃዎቹን ከተቀበለ ከአንድ ዓመት በኋላ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መብቱ ሊሰራበት ይችላል፣

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም ተቃራኒ የሆነ ደንብ ከሌለ ወይም በውሉ በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በቀር ዕቃው ሊበላሽ ወይም የዕቃው ዋጋ እርሱ በዕቃው ላይ ካለው የማገቻ መብት በታች ሊወርድ እንደሚችል ባለዕቃው ማከማቻ ቤቱ ማስረዳት ከቻለ ተገቢውን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ዕቃውን የመሸጥ መብት አለው። እንዲህም በሆነ ጊዜ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ሕግ ስለማካካሻ ሽያጭ የተደነገጉት ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ፣

፬· ዕቃውን ሲረከብ ባላወቀው እና ከዕቃው ዓይነት ወይም ባህርይ በሚነሱ ችግሮች የተነሳ በሰው ወይም በንብረት ላይ አደገኛ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል የተረዳ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ተገቢውን ማስጠንቀቂያ በዕቃ ላይ መብት አለን ለሚሉ ሁሉ በመስጠት ዕቃውን በግልጽ ጨረታ ወይም በግል ሊሸጠው ይችላል። ተገቢውን ጥረት አድርጎ ዕቃው አልሸጥ ካለው ዕቃውን በሌላ አመችና ሕጋዊ መንገድ እንዲወገድ ማድረግ ይችላል። ይህን በማድረጉም ኃላፊነት አይኖርበትም፣

፭· በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት ዕቃ የሸጠ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የራሱን የማከማቻና ሌሎች መሰል ክፍያዎች ከሽያጩ ዋጋ ላይ ቀንሶ የተረፈውን ለባለ መብቱ ተቀማጭ አድርጎ ማቆየት አለበት።

፲፰· የባለዕቃ ማከማቻ ቤት የማገቻ መብት

፩· ባለዕቃ ማከማቻ ቤት የማገቻ መብቱን በዚህ አዋጅ መሠረት ሊጠቀም ይችላል፣

፪· ዕቃውን በገዛ ፈቃዱ ለአደራ ሰጭው ያስረከበ ወይም አጥጋቢ ምክንያት ሳይኖረው ዕቃውን ያላስረከበ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት ሊያገኝ የሚችለውን የማገት መብት ያጣል።

፲፱· የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን የማገቻ መብት ተግባራዊ ስለማድረግ

፩· ሊከፈለው የሚገባው ማናቸውም ሕጋዊ ክፍያ እስኪደረግለት ድረስ አንድ ባለዕቃ ማከማቻ ቤት ባስቀመጠው ዕቃ ላይ የይገባኛል ጥያቄ የማንሳትና ዕቃውንም አግቶ የማቆየት መብት አለው፣

3) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) and (2) hereof, a warehouse operator may commingle fungible goods with other goods of the same kind, quality and grade in which case holders of the warehouse receipts for the commingled goods shall own the entire mass in common with each holder being entitled to claim such proportion thereof as the quantity shown by his receipt.

17. *Duration of Storage Agreement*

1) Upon termination of the period of storage stipulated in the warehouse receipt, a warehouse operator may, by serving due notice on the person on whose account the goods are held, his lawful representative or any other person known to have an interst in the goods, require payment of any charges due and removal of the goods represented by the warehouse receipt.
2) Where no definite term has been fixed for storage, the warehouse operator may avail himself of the rights specified under Sub-Article (1) hereof one year from the date of deposit.
3) Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) and (2) hereof, and in the absence of regulations or an agreement to the contrary, a warehouse operator may sell the goods where he can show that they are about to deteriorate or decline in value to less than the amount of his lien, subject to proper notification. The provisions of the 1960 Civil Code of Ethiopian on compensatory sale shall apply in such cases.
4) If on account of quality or condition of the goods of which he had no knowledge at the time of deposit, they are a hazard to persons or property, a warehouse operator may sell them at a public or private sale upon notifing persons known to claim an interest in the goods. He may dispose of them in any lawful manner and shall incur no liability by reason of such disposition where, after a reasonable effort, he is unable to sell them.
5) A warehouse operator effecting sale in accordance with the provisions of this Article may satisfy his lien from the proceeds and shall hold the balance at the disposal of the person or persons entitled to it.

18. *A Warehouseman's Right of Lien*

1) A warehouse may use his right of lien pursuant to this Proclamation.
2) A warehouse operator who voluntarily delivers the goods to the bailor or who fails to deliver the goods there being no valid reason justifying his act shall lose his right of lien under this proclamation.

19. *Enforcement of a Warehouseman's Right of Lien*

1) A Warehouse operator has a specific right of claim on the goods stored in his warehouse and may detain them until the claims for which the lien arises are satisfied.

፪· ይህንን መብቱን ተግባራዊ ለማድረግም በማከማቻ ቤቱ ከተቀመጡት ዕቃዎች መሀል ለሚጠየቀው ክፍያ የሚመጥኑትን ያህል በአካባቢው የንግድ አሠራር ተቀባይነት ባለው መንገድ በጨረታ ወይም በግል ሊሸጣቸው ይችላል፣

፫· ይሁንና ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) በተመለከቱት መብቶች ለመሥራት ከዚህ በታች ያሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለበት፣

ሀ) ለመብቱ መሠረት የሆኑት የዕቃ ማከማቻ ቤት የአገልግሎት ክፍያና ሌሎችም ሂሳቦች የመክፈያ ጊዜ የደረሰ እንዲሆን ያስፈልጋል፣

ለ) በዕቃው ላይ መብት አለን ለሚሉ ሰዎች ሁሉ ተገቢው ማስታወቂያ እንዲሰጣቸው ያስፈልጋል፣

ሐ) የሚላከው ማስታወቂያ የተጠየቀውን ክፍያ መጠን፣ ታግተው ያሉትን ዕቃዎች የሚያሳይ መግለጫ፣ ክፍያ የሚደረግበትን የተቀረጠ የጊዜ ገደብ እንዲሁም በተባለው ጊዜ ክፍያ ካልተፈጸመ ዕቃዎቹ በጨረታ ወይም በግል የሚሸጡ መሆናቸውን የሚያመለክት ማስገንዘቢያ የሚያካትት መሆን ይኖርበታል፣

መ) መብቱ ተፈጻሚ የሚሆነው በዕቃ አከማቹ ዘንድ ከተቀመጡና በይዞታውም ሥር ካሉ ዕቃዎች ለሚጠየቁ ክፍያዎች ብቻ ነው፣

ሠ) የማገት መብቱ ተፈጻሚ የሚሆነው ለይገባኛል ጥያቄው ምክንያት በሆነው በአንድ የተለየ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በተመለከቱት ዕቃዎች ላይ ወይም ከእነዚህ ዕቃዎች ሽያጭ በተገኘ ገንዘብ ላይ ብቻ ነው። መብቱ በባለዕቃ ማከማቻው ይዞታ ሥር በሚገኙ በሌሎች የአደራ ሰጭው ዕቃዎች ተፈጻሚ አይሆንም፣

፬· በሚሸጠው ዕቃ ላይ መብት አለኝ የሚል ሰው የባለዕቃ ማከማቻ ቤቱን የአገልግሎት ሂሳብና ሌሎች ተገቢ ወጭዎችን የሚሸፍን ክፍያ በማድረግ ሽያጩን ማስቆም ይችላል። እንዲህም ሲሆን ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ በዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ ላይ የተመለከቱትን የውል ቃላትና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት አድርጎ ዕቃውን ይዞ ይቆያል፣

፭· የማገቻ መብቱን ተግባራዊ የሚያደርግ ማንኛውም ባለዕቃ ማከማቻ ቤት በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተላልፎ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ለጉዳቱ ኃላፊ ይሆናል፡

፮· አግባብነት ያላቸው የግዴታዎች ሕግ ድንጋጌዎች የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ለማሟላት ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ክፍል አራት

## የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ስለማስተላለፍ

፳· ስለማስተላለፍ

፩· አንድ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የሚተላለፍ ወይም የማይተላለፍ ሊሆን ይችላል፣

፪· ማናቸውም የማይተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በላዩ ላይ "የማይተላለፍ" የሚል ቃል የያዘ መሆን አለበት። ይህ አነጋገር ካልተመለከተበት ደረሰኙ የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ይሆናል፣

፫· ከማይተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የሚመነጩ መብትና ግዴታዎች ለሦስተኛ ወገን የሚተላለፉት ሽያጭን ወይም መደበኛ የመብት ማስተላለፍን በሚመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ብቻ ነው፣

2) He may foreclose his lien by selling sufficient amount of the stored goods by public auction or private sale on such terms and upon such conditions as are commercially reasonable under the circumstances.

3) A warehouseman may, however, exercise his right under Sub-Article (1)and(2) hereof subject to compliance with the following conditions:

(a) the storage and other charges for which the right arises must be due:

(b) all persons known to claim an interest in the goods must be duly notified:

(c) the noification must include a statement of the claim, a description of the goods subject to lien, a demand for payment within a specified period of time and an indication that the goods will be sold by public or private sale if the claim is not paid within the time stated therein;

(d) the right should only be exercised with respect to claims in relation to the goods stored and in the possession of the warehouse operator;

(e) the lien holds good only as to the goods covered by the particular warehouse receipt out of which the right arises or on the proceeds thereof and not against any other property of the same bailor in the possession of the warehouse operator.

4) A person claiming a right in the goods may, at any time before the sale, pay the amount required to satisfy the lien and other reasonable expenses of the warehouse operator and stop the sale. The Warehouse operator shall in such cases retain the goods subject to the terms of the warehouse receipt and the relevant provisions of this Proclamation.

5) A warehouse operator who, in the course of exercising his right of lien. fails to comply with requirements stated hereof is liable for damages he causes to others.

6) The relevant provisions of the law of obligations may supplement the provisions of this Article.

## *PART FOUR*

## *Negotiation of Warehouse Receipts*

20. *Negotiation*

1) A warehouse receipt may be negotiable or non-negotiable.

2) A non-negotiable warehouse receipt shall always carry the words "Nonnegotiable" on the face of it. Failure to observe this rule shall have the effect of rendering the instrument negotiable.

3) Rights and obligations arising out of a non-negotiable warehouse receipt shall only be transferred to third parties in accordance with rules governing sale or those on ordinary assignment.

፬· የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ በጀርባ ፊርማ እና በቀጥታ በመስጠት ለሦስተኛ ወገኖች ሊተላለፍ ይችላል። በሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ላይ የተጻፈና የደረሰኙን ትልልፍ የሚገድብ ቃል ውጤት አይኖረውም፣

፭· ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደረሰኙ ላይ ፊርማን ብቻ በማኖር፣ ላምጪው የሚል ቃል ጽፎ በመፈረም፣ ወይም የተቀባዩን ስም ጽፎ በመፈረም የተቀመጠ የጀርባ ፊርማ ውጤት ይኖረዋል። ደረሰኙ ስም ተጽፎበት በጀርባ ፊርማ በሚተላለፍበት ጊዜ እንደገና ፊርማን ብቻ በማኖር፣ላምጪው፣የሚል ቃል ጽፎ በመፈረም ወይም የተቀባዩን ስም ጽፎ በመፈረም በጀርባ ፊርማ ሊተላለፍ ይችላል። ቀጣይ ትልልፎችም በተመሳሳይ መንገድ ሊደረጉ ይችላሉ፣

፮· ትክክለኛውን የማስተላለፍ አሠራር ተከትሎ በተሠራ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ መብት የተላለፈለት ሰው በደረሰኙ ላይ በተመለከተው ዕቃ ላይ ሙሉ መብት ይኖረዋል። ደረሰኙን በቅን ልቦና የያዘ ሰውም በደረሰኙ ላይ ያለው መብት ቀደም ሲል ከነበሩ ከማናቸውም መብቶችና መቃወሚያዎች ነፃ ይሆናል።

፳፩· ሌሎች ከዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ማስተላለፍ የሚመነጩ መብቶች

፩· የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን ጀርባ ፊርማ ለሌላ ያስተላለፈ ሰው ከእርሱ በፊት ደረሰኙን በጀርባ ፊርማ ያስተላለፉ ሰዎች ወይም ባለዕቃ ማከማቻ ቤቱ ለፈጸመው ጥፋት (ጉድለት) ኃላፊነት የለበትም ፣

፪· የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የተላለፈለት ሰው በስህተት ወይም በሌላ ምክንያት በደረሰኝ ሊገለጽ ይገባው የነበረ ፍሬ ነገር አለመገለጹን ካወቀ ይኸው እንዲገለጽለት በጀርባው ፊርማ ደረሰኙን ያስተላለፈለትን ሰው በማናቸውም ጊዜ ሊጠይቀው ይችላል ።

፳፪· ዋቢ ስለማለፍ

የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ዋጋ ተቀብሎ ያስተላለፈ ሰው ፣

፩) የዕቃ ማከማቻ ደረሰኙ እውነተኛ ስለመሆኑ ፣
፪) የደረሰኙን ሕጋዊነትና ያለውንም ዋጋ የሚያሰናክል ምንም ዓይነት ሁኔታ ለመኖሩ የማያውቅ ስለመሆኑ ፣ እንዲሁም
፫) ያደረገው ማስተላለፍ ደረሰኙን እና በላዩ የተመለከቱትን ዕቃዎች በተመለከተ ትክክለኛና ተፈፃሚ ስለመሆኑ ፣ ዋቢ ነው ።

፳፫· ቀሪ ስለሚሆኑ መብቶች·

፩· ከባለዕቃ ማከማቻ ቤትነት ሥራው በተደራቢ ተተካኪ ዕቃዎችን ለመሸጥ ፈቃድ ካለው ሰው በተለመደው የንግድ ሥራ አካሄድና በቅን ልቦና እነዚህን ዕቃዎችን ገዝቶ የተረከበ ሰው በዕቃ ላይ ከዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ የመነጨ መብት ካለውና ደረሰኙ በአግባቡ ከተላለፈለት ሰው ጥያቄ ነፃ ነው ፣

፪· እንደዚሁ ዓይነቱን የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ ዋጋ ሰጥቶ የተላለፈለት ሰው የሚኖረው መብት ደረሰኙን ያስተላለፈለት ሰው በሚኖረው መብት ላይ ብቻ የተወሰነ ይሆናል ።

፳፬· የዕቃ ማከማቻ ደረሰኞችን በመያዣ ስለመስጠት

፩· አንድ የሚተላለፍ የዕቃ ማከማቻ ደረሰኝ አምጭ የሆነ ሰው ደረሰኙን መያዣ በመስጠት ከባንክ ወይም ከተፈቀደለት መሰል አበዳሪ ተቋም ገንዘብ ለመበደር ይችላል፣

4) A negotiable warehouse receipt may be transferred to third parties by endorsement and delivery. A provision in a negotiable warehouse receipt that limits negotiability shall be of no effect.
5) For the purpose of this Proclamation, an endorsement may be in blank, to bearer or to a named person, and if the endorsement is to a named person the receipt may again be negotiated by endorsement in blank, to bearer or to another named person. Subsequent negotiations may also be made in like manner.
6) Due negotiation of a negotiable warehouse receipt shall have the effect of conferring full title over the goods represented by such instrument on the endorsee. The holder in due course shall enforce his right in the instrument free from all previous claims and defects.

21. *Other rights Arising out of Negotiation of Warehouse Receipts*

1) Endorsement of a warehouse receipt does not make the endorser liable for any default by previous endorsers or by the warehouse operator.
2) The transferee of a negotiable warehouse receipt may at any time require the transferor to supply the necessary endorsement which, by default or otherwise, is missing from the instrument.

22. *Warranties*

A transferor for consideration of a negotiable warehouse receipt shall waranty that:

1) the warehouse receipt is genuine;
2) he has no knowledge of any fact that would impair the validity and worth of the receipt; and
3) his negotiation is rightful and effective with respect to the title of the warehouse receipt and the goods it represents.

23. *Defeated Rights*

1) A good faith purchaser who, in the ordinary course of business. buys fungibles and takes delivery thereof from a warehouse operator who is also licensed to sell such goods takes the fungibles free of any claim under the warehouse receipt even though the receipt has been duly negotiated.
2) A transferee of a negotiable warehouse receipt who has taken it for consideration shall only acquire the title and rights of the transferor.

24. *Warehouse Receipts as Security Devices*

1) A holder of a negotiable warehouse receipt may borrow money from banks or similar authorized lending institutions by offering such receipt as collateral.